# ሰባተኛው መልአክ

ከስብሐት ገብረ እግዚአብሔር



2059

NH
bate

http://ethioliberty.wordpress.com/

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

# ሰባተኛው መልአክ

ግንቦት 2000 - አዲስ አበባ

http://ethioliberty.wordpress.com/

© የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

All rights reserved

የመጀመሪያ ዕትም - 1992

ሁለተኛ ዕትም - 2000

አሳታሚ፡- ቃልኪዳን ታደሠ

የሽፋን ስዕል፡- ታምራት ገዛኸኝ

የውስጥ ዲዛይን ገጽ ቅንብር

ማኅቤት አሳታሚ



## እንደ መግቢያ

ውድ አንባብያን

ይኼ መግቢያ ከዚህ ለምታነቡት «ሰባተኛው መልአክ» ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት ላነበባችሁት ‹የተኳሳሽ› ወይም ‹የተበረዘ› እትምና በቅርብ ጊዜ ‹እንደወረደ› ለምናትመው «ትኩሳት» ጅምር ያገለግላል የሁለቱም ልቦለዶች መቸቻያው በመሆኑ፣ ይዘታቸው ይለያያል'ንጂ

የሰው ልጅ በመንግሥት ደረጃ ተደራጅቶ መኖር ከጀመረባቸው ዘመናት ወዲህ እና ቋንቋን በፅሁፍ አስፍሮ ለመጠቀ ትውልዶችን ማስተላለፍ ከቻለ ወዲህ፣ የትም አገር ይሁን፣ በመጀም ዘመን



http://ethioliberty.wordpress.com/

ይሁን፤ የሚከተለው ተደጋጋሚ ድራማ ይከሰታል።

ስልጣኑን ሶስት የተደራጁ ሀይሎች ይጋሩታል። ሰፊው ህዝብ እንደሆነ ዘንታለሙን በስንትና ስንት ታታሪነት <ጥሮ ግሮ> ይኖራል። እንደፈረደበት ደግሞ እነዚህን ሀይሎች መደዳውም መካሁም እንደየፍላጎታቸው ያገለግላቸዋል፤ ያቀማጥላቸዋል፤ ይሞትላቸዋል [እነሱ ተፎካካሪዎቹ እርስ በርስ እየተቃወሙ፤ በጉ ህዝብ ግን ሳያውቅ-ባቸው እየተቀራመቱት]

ሀ) መንፈሳዊ [ሀይማኖታዊ ወይም ርእዮተ አለማዊ] ስልጣን በዚህ በእውነታዊ ፍርሀቶቹን ዘመን እና በቀላው ገፀባህሪያቶችን አገር ከቤት እንስሳት ይሰርቃል

ለ) ወታደራዊ ስልጣን በጦር ሀይሎች አዛዦች ስልጣን ይተኩሳል

ሐ) ኢኮኖሚያዊ ስልጣን ከገንዘብና ትርፍ ማስገኛዎች ትስስር፤ እና ገንዘብ ከሚገኘው ሰው ሰራሽ ትእምር ይመነጫል

ይህ መጣጥፍ የሚመለከታቸው የሁለቱ ስርአቶች ገፀባህሪያት ፔስት ተማሪዎች ስለሆኑ፤ እና ሁለቱም Marxist በመሆናቸው፤ በማርክሳዊ እቅድ ገንዘብ ምን እንደሆነ እነሆ፡-

እንበል እንጂ የመቶ ብር note ይዤ ልውጣ። ወርቅ ቶኛው በኢትዮጵያ-ዊ ጎሬ እዴን ብሰጠው። በማህበረሰብ

እየደን ስናውቀውና ስንሰራበት ግን ሌላ ነው





http://ethioliberty.wordpress.com/

ምግብ ቤት ቁርሴን በልቼ፣ ያቺን መኖ
ሪያቼ፣ መልሶን ዘመና ተቀብዬ እወጣለሁ።
በሌሊት ሌመዳጄ ተለጎልሞ፣ ዳበዳቤ እል-
ካለሁ — ወይ ሰልፍ እደውላለሁ። መልሶን
ሰማንያ ከምናምን ተቀብዬ ወጣቼ፣
በኦቶቡስ ወይ በታክሲ መርካቶ ነኝ
... እስክ መጠለርቻ ሳንቲም እኔ
መቶ ብር ስንት magic እንደምትሰራ-
ልኝ ይታያኛሁ። እዚያ ሄዳ ደም ለሎች
ሰዎች ሌሎች ተአምራት...

እስከዛሬህ ድረስ ‹ታክ ሳት› እና
‹ሰገተኛው መልእክ› ተመሳሳይ ናቸው።
በአንድ መፅሀፍ ለተጠቃለሉ ነበር። ግን
መጠሌታቸ የሆነ ለይነት አላቸው

እንዴቸውን የሚያመሉቸው የፍቅር
መንፈስ... ውበት አዎንታዊና
እስደሳች



ሌላቸውን የሚነኳቸው የጥጎቹ
መንፈስ... ውበት አሉታዊና
አሳዛኝ

ከእንጅ መልካም ደስታ
ከሌላው መልካም ሀዘን
እመኝላችኋለሁ
ስብሐት ለአብ



http://ethioliberty.wordpress.com/

# አንድ

ፈረንሳይ አገር በምማርበት ጊዜ፡-

አንድ አመት ያህል ከአየለ ነብር ጋር አሳልፌአለሁ፡፡ ንዴቱ በቶሎ ስለሚገነፍል እዚያ ዩኒቨርሲቲ የምንማር ሀበሾች ነብር እንለው ነበር

ያን ጊዜ አየለ ነብር ከእኔና ከያሲን በቀር ሰው አያስጠጋም ነበር፡፡ ለምሳሌ አንድ ቀን ብቻውን «ሴንትራ» የተባለው ካፌ (ቡና ቤት) ውስጥ ቁጭ ብሎ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ይገባና «coffee, coffee, coffee!» ይሰናል:: ያሲን ተነስቶ ቡና ይጥዳል

አየሰና ያሲን ስለኮሙኒዝም ማውራት ይጀምራሉ



# ሁለት

በምሳና በአራት ሰዓት ያሲን ይሄድና ዩኒቨርስቲው በር አጠገብ አንዲት ዛፍ ስር ይቆማል:: የሚያውቁት ተማሪዎች ሁሉ ለምን እዚያ እንደሚቆም ያውቃሉ! ምሳውን ወይም እራቱን የሚያበላው ሰው ፍለጋ ነው:: ጠርተው ያበሉታል:: በጣም ውብ ስለሆነና በጣም ተወዳጅ ስለሆነ ያበሉታል (ከፈረንሣይ መንግሥት እንደኛ እስኮላርሽፕ የለውም:: ከሀገሩም ገንዘብ የሚልክለት ሰው የለም)

ማታ ጥሩ ፊልም ያለ እንደሆነ ያሲን ይሄድና ሲኒማው በር ላይ ይቆማል:: የሚያውቁት ተማሪዎች



http://ethioliberty.wordpress.com/

እርጥብ ሙቀት ውስጥ አስገባችኝ፡፡ ተራውን አፏን እንዲልሳት አንገቷን ወደሱ አዞረችለት፣ እኔ አንድ ጡቷን ጎረስኩት

ትንሽ እንደቆየን

«ልዙርልህ?» አለችው

«አልፈልግም» አላት

«እርግጠኛ ነህ?» አለችው

«እንዲህ ይሻለኛል?» አላት

«ተው. . . ቀስ በል . . . ቀስ. . . እንደሱ!» አለችው እያቃሰተች ከው አልኩ፡፡ እኔ ከፊቷ እንደገባሁ እሱ ደግሞ ከኋላዋ ገብቷል! የነገሩ እንግዳነት ለጊዜው አሸነፈኝ፡፡ ቀላዩ ውስጧ እንዳለ ድንገት ሞተብኝ፡፡ ነገሩ ገብቷት ይሁን በአጋጣሚ ይሁን እንጃ፣ አፏን አፌ ላይ ደቀነችና በጣም ሀይለኛ የሆነ እርጥብ አሳሳም ትስመኝ ጀመር፡፡ የሞተው ቀላዩ እንደገና ነብስ ዘራ፡፡ ትንሽ ቆይቼማ ያሲን ከኋላዋ እንደከተተባት ሳስብ ጊዜ ስሜቴ እየበረታብኝ፣ እንደ አንበሳ ሀይለኛ እየሆንኩ ሄድኩ

በህይወቴ እንደዚያች ያለች ሌሊት አሳልፌ አላውቅም፡፡ የብልግናን ውበት፣ የቆሻሻነትን ክብር ለመጀመሪያ ጊዜ መገንዘቤና መቀበሌ ነበር፡፡



ጧት ስነቃ እነሱ ወደ ያሲን ክፍል ሄደዋል፣ ብቻየን ነኝ፡፡ ያለፈው ሌሊት ትዝ አለኝ፡፡ ላምነው አልቻልኩም፡፡ ግን የአልጋው ሽታ አለ፣ እንሶሳውም ተጨማልቋል፡፡ አይኔን ዘጋሁ፡፡ እንቅልፍ እንደገና ወሰደኝ

ከዚያ በኋላ የያሲን፣ የአይሪንና የኔ ህይወት ሌሊት ሌሊት አንድ አልጋ ውስጥ ይገመድ ይገማመድ ይፍታታ ጀመር



http://ethioliberty.wordpress.com/

# ሶስት

ቀን ሲሆን አይሪን ወደኛ አትመጣም፤ ቀን ሲሆን ወደኛ የሚመጣው አየለ ነብር ነው

ይመጣና «coffee, coffee, coffee,» ይለናል፡፡ ያሲን ተነስቶ ቡና ይጥዳል፡፡ አየለና ያሲን ሲጋራ እያጨሱ ቡና እየጠጡ ስለኮሙኒዝም፣ ስለካፒታሊዝም፣ ስለኢምፔሪያሊዝም ማውራት ይጀምራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ አብሬአቸው እወራለሁ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን ዝም ብዬ ነው የማዳምጣቸው

ያሲን ድሮ ኮሙኒስት ስለነበረ ስለኮሙኒዝም ብዙ ዕውቀት አለው፡፡ ግን አሁን ኮሙኒዝምን እንደ ዘመናዊ ሃይማኖት ነው የሚቆጥረው፡፡ እንደ ሌላው



ሃይማኖት ሁሉ፣ ኮሙኒዝምም የራሱ አማኞችም አሉት፣ ቄሶችም አሉት፡፡ ልዩነቱ የኮሙኒዝምን መንግስተ-ሰማያት በህይወታችን ነው የምንወርሳት፡፡ ወደ ምድር አወረዳት እንጂ ሃይማኖት መሆኑ አልቀረም፡፡ የሌሎች ሃይማኖቶች ወግ እንዳይቀርበት እንኳ እርስ በርሱ በእምነት መከፋፈልና መወጋገዝ ጀምሯል፣ ይላል ያሲን

አየለ ግን የጋለ፣ የተናደደ ኮሙኒስት ነው፡፡ በመጀመሪያ ነገር የአሜሪካኖቹና የምዕራብ አውሮፓው ያኖቹ ኢምፔሪያሊዝም (ወይም ቅኝ ገዢነት) ያናድደዋል፡፡ ቀጥሎ አሜሪካንና ምዕራብ አውሮፓን እየታዘዙ እየተሽቆጠቆጡ የሚኖሩት የአፍሪካ፣ የእስያና የደቡብ አሜሪካ መንግስታት ያናድዱታል፡፡ ቀጥሎ የክሩሽቾቭ ሪቪዥኒዝም እና የሶቪየት ሕብረት ከአሜሪካ ጋር ተቻችሎ መኖር ያበሳጨዋል፤ በተለይም እነ ክሩሽቾቭ የስታሊንን ሬሣ ሌኒን አጠገብ ከተቀበረበት ክክብር ቦታው (ከስመ ገናናው ቀይ አደባባይ) ቆፍረው አውጥተው ስላዋረዱት በጣም ይበሽቃል፡፡ «And now, for the pleasure of the American imperialist, fat ballerinas like Kruschev are dancing and farting over stalin's grave!» ይላል፡፡ ትልልቅ አይኖቹ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ውስጥ የቁጣ ነበልባል ይቀጣጠላል። ከዚያ እንግዲህ ስለአሜሪካኖቹ ውድቀትና ስለኮሙኒዝም ድል አድራጊነት ይተነብያል

«የአሁኑ የሶቪየት ውጊያ ዩ.ኤስ.ኤ የተባለውን የበሰበሰ ዛፍ ቆርጦ የሚጥል የመጀመሪያው የምሳር ምት ነው!» ይላል

አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ወደ ዩኒቨርስቲው ምግብ ቤት እናመራለን

እንግዲህ አየለ ትላንት ማታ እራቱን እንደበላ ሌላ እህል አልቀመሰም። ዓመቱን ሙሉ እንደዚህ ነበር። አንዳንድ ቀን ከኔና ከያሲን ጋር (አንዳንዴም ከሌሎቹ ሀበሾች ጋር) እራት ይበላል

ከእራት በኋላ ካፌ ዶርቢቴል የተባለው የተማሪዎች መሰብሰቢያ ካፌ ይሄድና ቡና እየጠጣ ስለኮሙኒዝም ወይም ስለ ጥቁሮች መጨቆንና መጠቃት ይከራከራል። ካገኘው ሰው ጋር ይከራከራል። ብቻ ነጭ አይሁን፤ በተለይም አሜሪካዊ አይሁን። ወደ ሶስት ሰዓት ላይ ሌሎቹ ተማሪዎች ወደየጥናታቸው ወይም ወደየሲኒማቸው ይሄዳሉ

እኔ ሲኒማ ከገባሁ አየለ ፥ብሮኝ ሲኒማ ይገባል፤ እኔ ወደ ጥናት ከሄድኩ እሱ ወደካፌ



«ሴንትራ» ይሄዳል። ከኔ ጋር ሲኒማ ከገባ ከሲኒማ መልስ (ወደ እኩለ ሌሊት ላይ) እኔ ወደ መኝታዬ ስሄድ እሱ ወደ ካፌ ሴንትራ ይሄዳል። ግራም ነፈሰ ቀኝ፣ አየለ ሌሊቱን የሚያሳልፈው ካፌ ሴንትራ ውስጥ ነው

ይሄ ካፌ ሴንትራ የሌሊት መጠጊያ ነው። እንቅልፍ እምቢ ያላቸው ጐረምሶች፣ ከባሎቻቸው የተጣሉ ሴቶች፣ ሌሊት እረፍት የነፈጋቸው ሰዎች እዚህ ካፌ ቁጭ ብለው እየጠጡ፣ የግል ሀሳባቸውን እያሰቡ፣ ወይም የጋራ ሀሳባቸውን እየተወያዩ፣ ፀሐይዋ እስክትወጣላቸው ይጠብቃሉ። አብዛኛዎቹ ግራ የገባቸው፣ ህይወት ያስደነገጣቸው፣ ኑሮ የከበዳቸው፣ እንቅልፍ የሸሻቸው የሌሊት ሰዎች ናቸው

አየለ ሁለት ፓኮ ሲጋራ ይገዛና ለብቻው አንድ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብሎ ሲጋራውን እያጨሰ፣ ጋዜጣ መፅሔት ወይም መፅሐፍ እያነበበ ሲጠጣ ያመሻል። ወደ አስራ አንድ ሰዓት ላይ የሚያነበው ነገር አልገባ ሊለው ይጀምራል፤ ስካር እንጉሉን ይሸፍነዋል። አሁን እንግዲህ እንቅልፍ ሊወስደው ይችላል። ሂሣቡን ከፍሎ ወደ ዩኒቨርስቲ ይሄዳል። (ሲራመድ ፈፅሞ አይንገዳገድም) መኝታ ቤቱን ይከፍታል፤ አልጋው



http://ethioliberty.wordpress.com/

አንድ ጥቁር አየለን ውሃና ጨው ወይም ዳቦ አቀብለኝ ያለው እንደሆነ አየለ በጨዋ ደምብ ያቀብለዋል፡፡ እሱም ሲያስፈልገው ጥቁሩን አቀብለኝ ይለዋል፡፡ አንድ ፈረንሣዊ አቀብለኝ ያለው እንደሆነ ወስዶ ፊቱ ላይ ይደቅንለትና አንድ ጊዜ ያፈጥበታል

እንግዲህ አሜሪካኖቹ ፈረንሣይኛ ሲናገሩ ከአጣጣላቸው ያስታውቃል፡፡ ታዲያ ውሃ ዳቦ ጨው አቀብለኝ ያለው አሜሪካዊ ከሆነ አየለ ልክ እንዳልሰማ ሰው ዝም ብሎ መብላቱን ይቀጥላል፡፡ አሜሪካዊው ጥያቄውን የቀጠለ እንደሆነ አየለ እኔን «ይኼ ነጭ ቂጥ ባሪያውን አጥቷል?» ይለኛል፡፡ ቁጣ ፊቱን ያለብሰዋል፡፡ አሜሪካዊው የፈለገውን እኔ አቀብለዋለሁ፡፡ እኔ ርቆብኝ ልሰጠው ካልቻልኩ እንደገና አየለን እባክዎን ያቀብሉኝ ይለዋል፡፡ አየለ በቁጣ የጠቆረ ፊቱን ያዞርና ንዴት የሚውለበለብባቸውን ትልልቅ አይኖቹን ይተክልበታል፡፡ ቃል አይናገርም፡፡ ብቻ በአይኖቹ እሣት ይገርፈዋል

«አየለ!» እለዋለሁ

ወደኔ ፊቱን ያዞራል

«እንግዲህ ክብርህን ጠብቅ» እለዋለሁ

«ታዲያ እኔ የማንም ነጭ አሽከር ነኝ?!» ይለኛል



«እሱ ቢሆን ያቀብልህ ነበር፡፡ አሁን ህፃንነቱን ተወውና አስተዳደግህን አስታውስ፡፡ በጨዋ ደምብ የጠየቀህን በጨዋ ደምብ አቀብለው»

የተጠየቀውን እቃ አንስቶ ጠያቂው ፊት ላይ ገጭ አድርጎ ያስቀምጥለትና መብላቱን ይቀጥላል



http://ethioliberty.wordpress.com/

# አራት

አንድ ቀን ያሲን «ስለ አየለ ነገር እንዴት ይሻላል?» አለኝ

«እንዴት ማለት?» ብለው

«አንድ ቀን ራሱን እንዳይገድል ፈራሁ» አለኝ

«ለምን ራሱን ይገላል?»

«ጥላቻ በዛበታ! ይህን ሀገር ወይም ይህን ሰው እወዳለሁ ሲል ሰምተኸው ታውቃለህ? እሱ የሚያስበውና የሚናገረው ስለሚጠላቸው ሀገሮች ብቻ ነው። አሜሪካኖችን ይጠላል! ነጮችን ይጠላል! አረቦችን ይጠላል! ሌላ ቀርቶ ሀበሾችንም ይጠላል።



ካንተ በቀር ማንንም ሀበሻ አይጠጋም። እኔን የሚጠጋኝ ካንተ ጋር ስለሚያገናኝና ስለኮሙኒዝም ከሱ እኩል ስለማውቅ ነው። ግን ኮሙኒዝምን አይወድም»

«እንዴት?»

«እሱ ኮሙኒዝምን የሚቀበለው አሜሪካኖቹንና ምዕራብ አውሮፓውያንን የሚያጠፋ መሣሪያ ሆኖ ስለሚታየው፤ ሀብትን ከሀብታሞች ነጥቆ ሀብታሞችን የሚያጉሳቁል መስሎ ስለሚታየው ነው እንጂ እውነተኞቹ ኮሙኒስቶች እንደሚያምኑት ኮሙኒዝም ለሰው ልጆች እውነተኛ መድኃኒት ነው ብሎ ስለሚያምን አይደለም። ይገባሃል የምልህ?»

«ይገባኛል»

«አስተውለሃል? ጥላቻ ብቻ ነው እፊቱ ገፅታ ላይ ጉልቶ የሚታየው። በጥላቻ ህይወቱን እያቃጠለ ይኖራል። ምክንያቱም ራሱን በህይል ስለሚጠላ ነው»

«ለምን?»

«ራሱን ይጠላል» አለ ያሲን «ለምን መሰለህ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ የሚበላው? ለምን መሰለህ ከሲጋራና ከመጠጥ ጋር ብቻ የሚኖረው? ለምን መሰለህ መኝታ ቤቱ ውስጥ ተዘግቶ ታፍኖ ቆሻሻ መሀል ተኝቶ የሚውለው? ራሱን ለመግደል ነው።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ለምን መስለህ አጋጣሚ ባገኘ ቁጥር አሜሪካኖቹን የሚገሳምጣቸውና ነገር የሚፈልጋቸው?»

«ለምንድነው?»

«ስለሚጠላቸው ሊሰድባቸው ሊያዋርዳቸው ሊደበድባቸው ሊገድላቸው ሊያጠፋቸው ይፈልጋል። ግን ሌላ ፍላጎትም አለው»

«ምን ሌላ ፍላጐት?»

«እነሱ ደብድበው እንዲገድሉት ይፈልጋል»

«ትቃዣለህ?» አልኩት

«ዝም ብለህ አስተውለውና አለመቃዠቴን ታያለህ። ሲግሞንድ ፍሮይድን ብታነብ ስለ አየለ ብዙ ነገር ይገለፅልሃል»

«እሺ፣ እንደ አንተ ሀሳብ አየለ ለምንድነው ራሱን የሚጠላው?»

«ሀበሻ ስለሆነ ነው»

«አሁንስ ቅዠቱ እየባሰብህ ሄደ»

«በጭራሽ»

«አስረዳኝ እስቲ?»

«የናንተ የሀበሾች ኑሮ ወንድ ለወንድ መዋደድን በጣም ከመጥላቱ፣ ከመናቁ የተነሳ፣ ተራው ሀበሻ ወንድ ለወንድ መዋደድን እንደ ትልቅ



ሀጢአት፣ እንደ ዋና ውርደትና እንደ ቀፋፊ እፍረት ይቆጥረዋል።እውነቱን አይደለም?»

«ነው»

ግን በሰው ልጆች መካከል፣ በየትኛውም ዘመን በየትኛውም ህዝብ፣ አንዳንድ የተለዩ ወንዶች ይገኛሉ። ከአፈጣጠራቸው ይሁን ወይስ ከአስተዳደጋቸው ወይስ ከሁለቱ ይሁን እንጃ፣ ገላቸውና መንፈሳቸው ወንድን እንጂ ሴትን አይወድም»

«እሺ»

«አየለ ከእንዲህ አይነቶቹ ሰዎች አንዱ ነው። ታዲያ እጣው ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወለደ። ስለዚህ እንዲህ አይነት ሰው በመሆኑ ራሱን ይጠላል፣ ይንቃል። ልብ አድርግ፣ ይኸ ሁሉ ለአየለ በግልፅ አይታየውም። ሀበሻ በመሆኑ እንዲህ አይነቱን ነገር ስለ ራሱ በግልፅ ለማሰብ አይችልም። ስለዚህ ይህ ሁሉ ውስጡ ሲያድግ ለራሱ አይታየውም። ገባህ?»

«የምትለው ይገባኛል፣ ግን በሀሳብህ አልስማማም። ጥላቻ በዛበት የምትለው እውነት ነው። ራሱን ስለሚጠላ እንደ ሻማ በቀስታ ሀይወቱን እያቃጠለ ይጨርሳል የምትለው እውነት ሊሆን ይችላል። ወንድ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ይወዳል ስለምትለው ግን በጭራሽ አልስማማም፡፡ እንዲያውም ሳስብበት የነበረ አንድ ነገር አለ››

«ምን?» አለ ያሲን

«አንዲት ጥሩ ልጅ አግኝቶ አንድ ወር ያህል ቢተኛትና ቢደሰትባት ይህ ጥላቻው በጣም ይቀንሳል፣ ከአለም ጋር ይታረቃል፡፡ ስለዚህ አንዷን ቀስ ብለን እናያይዘው»

ያሲን ራሱን እየነቀነቀ «አንተም ራስህ ሀበሻ በመሆንህ እዚህ ውስጥ የማይታይህ ነገር አለ» አለኝ

«ምንድነው እሱ?» አልኩት

«እየለ የሚወደው አንተን ነው››

ድንግጥ አልኩኝ፡፡ ግንባሬ ላይ ላብ መጣ፡፡ ያሲን ሳቅ እያለ «አይዞህ! አንተ ወንድ ወዳጅ አይደለህም»

በኋላ ስለ ያሲን ብዙ አስብ ጀመር፡፡ ማነው ይሄ ያሲን? እሱ ሰውን ይወዳል፣ ሰውም እሱን ይወደዋል፡፡ ስለዚህ ኑሮ ወንዝ ውስጥ እንደሌሎቻችን ሳይፍጨረጨር በሰላም ይንሳፈፋል፡፡ አብረኸው ስትሆን ከንፁህ ሰው ጋር እንደሆንክ ይሰማሀል፡፡ ግን ይሄ ሰውዬ ማን ነው?

ምናልባት አይሪን ታውቀው ይሆን?



አንድ ማታ እኛ ቤት መጥታ (ያሲን አልነበረም) አልጋዬ ውስጥ ገብተን ስናወራ «ላንቺ እንደሚታይሽ ያሲን ማነው?» አልኳት

አረንጓዴ አይኖቿ የባሰውን ፈዘዙ፣ ቀጫጭን ረጃጅም ጣቶቿ መሀል ከተቀረቀረው ሲጋራ ጢሱ እየኮራ እየተንቀባረረ ወደ ላይ ይመዘዛል ይጠማዘዛል፡፡ ምላሷ ብቅ ብሎ ወፍራም ቀያይ ከንፈሮቿን ልሶ ተመለሰ፣ የረጠቡ ከንፈሮቿ ሳመል ከፊት ብለው፣ ትንንሽ ጥርሶቿን ያሳያሉ፡፡ መልኳ የት ላይ እንደሆነ ማየት አልቻልኩም፣ ግን እንደሷ ያሉ ውበት ያጥለቀለቃቸው ሴቶች በብዙ እንደማይገኙ እርግጠኛ ነበርኩ

ወርቅ መሣይ አጭር ፀጉሯን በአንድ እጇ ወደ ኋላ ገፋችው (ልማዷ ነው) «ያሲን ሊቅ ነው» አለችኝ «እውነተኛ ሊቅ ነው፡፡ ማለቴ፣ ዕውቀትን የሚገበየው ያንን ዕውቀት በስራ ላይ አውሎ ገንዘብ ወይም ስልጣን ወይም ዝና ለማግኘት አይደለም፡፡ ለማወቅ ብቻ ሲል ነው፡፡ ማወቅ፡፡ እለቀ በቃ፡፡ እና በጣም አዋቂ ነው»

‹‹እንዴት ማለት! በጣም አዋቂ?››



http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ለምሳሌ በፍልስፍና ሊሳንስ አለው። አሁን ደሞ ይሄ አመት ሲያልቅ በሃይማኖት ጥናት ሊሳንሱን ያገኛል። አረብኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሣይኛ ያውቃል። ማወቅ ስልህም አጠናቆ ነው። በፊት ኮሙኒስት ነበር፣ ግን ሰላማዊ በመሆኑ ከኮሙኒስቶች ጋር አልተስማማም። አጉል እምነትም የለው፣ ሃይማኖትም የለው። አሁን ምን በማድረግ ላይ እንዳለ ልንገርህ?»

«ንገሪኝ»

«እውነትን በመፈለግ ላይ ነው። እና እውነትን የት ነው የሚፈልጋት መሰለህ?»

«የት ነው የሚፈልጋት?»

«ግብረ ስጋ ውስጥ። የጥንት ሰዎች እምስንና ቁላን ያመልኩ ነበር። ለምን? የህይወት ምንጭ እምስና ቁላ ስለሆኑ። የህይወት እውነቱን ለማወቅ ወደ ምንጩ እምስና ቁላ መመለስ ያስፈልጋል። እኔ ስለው ቅጥ የሌለው መዘባረቅ ይመስላል። ያሲን ሲለው ግን ውበትም እውነትም እንዳሉበት ይሰማሀል።››

‹‹ቀጥይ››

‹‹እንስሳት የሚያምሩት መቼ ነው? የስሪያ ወራት በደረሰ ጊዜ ነው። የሰው ልጆች በምን እድሜ ነው ከሁሉ ይበልጥ ውብ የሚሆኑት? በጉርምስናቸው



እድሜ ነው (በሚባዱበት ዕድሜ) ዛፎችና ሌሎች አታክልት ምናቸው ነው ውብ? አበባቸው ነው። አበባቸው ምንድነው? ለእነሱ እምስና ቁላቸው አይደለም እንዴ? ለዚህ ነው ያሲን እውነትን ግብረስጋ ውስጥ የሚፈልጋት። ልገልፅልህ የፈለግኩትን ለመግለፅ የቻልኩ አይመስለኝም፣ ብቻ. . .»

«በመጠኑ ገልፀሽልኛል። ቀጥይልኝ»

«አንድ ሌሊት እኔንና አንተን አልጋ ውስጥ አላገኘንም? ታስታውሳለህ?»

«አ...ሀ»

«እኔ በሩን ስላልቆለፍኩት ነበር። አውቄ ነበር ያልቆለፍኩት»

«ለምን?»

«ያሲን ነው አትቆልፊው ያለኝ»

«እርግጠኛ ነሽ?»

«ገና እኔና አንተ መተኛት ሳንጀምር ያሲን እንደምንተኛ ያውቅ ነበር»

«እንዴት አርጎ?»

«እሱ ነዋ እንድተኛህ የጠየቀኝ»

«ለምን?»

«እርግጠኛ አይደለሁም»

«የሚመስልሽን ንገሪኝ እስቲ»



http://ethioliberty.wordpress.com/

«እንዴት ማለት እኒን?››

«በጣም ደስ ትሰዋለህ፡፡ ለኔ ደስ የምትለኝን ያህል ለሉም ደስ ትለዋለህ››

‹‹ምን ማለትሽ ነው?››

‹‹እንድታቅፈው እንድትስመው እንድትተኛው ይፈልጋል››

‹‹ምንድን ነው የምታወሪው?››

‹‹አላወቅክም ኖሯል?››

‹‹አላወቅኩም››

‹‹እውር ነህ፡፡ አይንህን ክፈት፡፡ ምን እንደሚፈልግ ልንገርህ?»

«ንገሪኝ»

‹‹እኔ ሁለታችሁ መሀል እሆን የለ? እሱም ተራውን መሀላችን ለመሆን ይፈልጋል፡፡ እሱ እኔ ውስጥ ሲገባ አንተ ደግሞ እሱ ውስጥ እንድትገባ ይፈልጋል››

‹‹ለምን?››

‹‹እንደዚህ ነዋ! እሱ ወንድም ሴትም ይወዳል፡፡ እኔ የምወደድ ዓይነት ሴት ነኝ፡፡ አንተ የምትወደድ ዓይነት ወንድ ነህ፡፡ ስለዚህ ሁለታችንንም ይፈልጋል፡፡ አስታውስ እሱ እንደኔና እንዳንተ ተራ



ሰው አይደለም፡፡ በሱ ዓይን አፍረት ወይም ፀያፍ የሚሉት ነገር የለም››

ያለችኝን ለሶስት ስናደርገው ታየኝ፡፡ አልቀፈፈኝም፡፡ በሀሳቤ የያሲንን ገላ አየሁት፡፡ ብዙ ጡንቻ የለውም፣ ፀጉር የለበትም፣ አነስ ያለ ውብ ገላ ነው፡፡ በሀሳቤ አቀፍኩት፡፡ አልቀፈፈኝም፣ ግን ከዚህ በፊት ስለ ወንድ እንዲህ ዓይነት ሀሳብ መጥቶልኝ አያውቅም

‹‹ለምን ይመስልሃል ይሄን ሁሉ የምነግርህ?››

«ለምንድነው?»

«ለያሲን ብዬ ነው»

«ትወጅዋለሽ?»

«መውደድ ብቻ አይደለም፡፡ አመልከዋለሁ፡፡ ታደርግለታለህ?››

«አልችልም» አልኳት

በሀሳቤ ግን እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ ዝም ብለን ቆየን፡፡ ያሲን ስለ አየለ ሲያዋየኝ አየለ ይወድሃል ብሎኝ ነበር፡፡ ምናልባት ሳይታወቀው የራሱን ስሜት አየለ ላይ ለጥፎበት ይሆን? አይሪን ስለያሲን የነገረችኝ በገዛ ራሷ ተነሳስታ ይሆን? ወይስ ራሱ ልኳት ይሆን? ለመሆኑ እቺ አይሪን እንዴት ያለች ሴት ነች?



http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ያሲን ቅዱስ ከሆነ አንቺ የሱ ደቀመዝሙር መሆንሽ ነዋ››

‹‹የሱ ደቀመዝሙር ለመሆን አልበቃም:: ምክንያቱም ልቤ የተራ ሰው ልብ ነው:: ከደግ ይልቅ ክፉን ይመርጣል:: ነፃነቱን በይሉኝታ ገበያ ይሸጣል››

የአሁኑ አነጋገሯ የእንግሊዝ ሳይሆን የምስራቃውያን ዘዬ አለው:: ከያሲን የወረሰችው አነጋገር መሆን አለበት

‹‹እንግዲያውስ ምኑ ነሽ?›› አልኳት

‹‹እንደ አገልጋዩ ልትቆጥረኝ ትችላለህ:: እስካሁን ያገኘሁት ሰው ሁሉ ሲያገለግለኝ ነው የኖርኩት:: ለወላጆቼ አንዲት ብቻ ስለሆንኩ እነሱ አገለገሉኝ:: እንደምታውቀው ረጅም ቀጭን አስቀያሚ ቢጤ ነኝ:: ግን እስከአሁን ያወቅኳቸው ወንዶች ልክ የውበት ንግስት እንደሆንኩ ያህል ተገዝተውልኛል፣ አገልግለውኛል:: ብቻ ምን ልበልህ፣ በሄድኩበት እንደተገለገልኩ ነው:: እና አሁን ያሲንን ማገልገል ለኔ ህይወት በቂ ለውጥ ነው::››

ሲጋራዋን በረጅሙ ሳበች፣ አይኗን ዘግታ ቆየችና ጪሱን ወደውጭ ተነፈሰች፣ ቀጠለች ‹‹ከያሲን ጋር ስሆን ሁሉ ነገር ንፁህ ነው:: ከሱ ጋር ብዙ



ግንኙነት ያደረኩ እንደሆነ ምናልባት ከንጽህናው ትንሽ ይተላለፍብኝ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: በብዙ ከሱ ጋር ያወራሁ እንደሆነ ከደግነቱ ትንሽ ያካፍለኛል ብዬ አምናለሁ

‹‹አየህ፣ በኛ ስልጣኔ፣ ይልቁንም በኔ ቤተሰብ አካባቢ፣ ግብረስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት፤ እንደ ሀጢያት ነው የሚታየው:: ስለዚህ ያሲንን ከማወቁ በፊት ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት ሆኖ ባይታየኝም እንኳ እንደ ጥሩ መልካም ነገር አልቆጥረውም ነበር

‹‹ከያሲን ጋር መተኛት ከጀመርኩ በኋላ ግን ግብረስጋን በአዲስ አይን አየው ጀመር:: አሁን ለኔ ግብረስጋ ንፁህ ውብ ነገር ነው:: የህይወት ዳንስ ነው:: በማንኛውም አይነት ብንደንሰው እወዳለሁ:: አብሮኝ የሚደንሰው ወንድ ልበ ንፁህ ይሁን እንጂ በኔ ገላ የፈለገውን ቢሰራ ደስ ይለኛል:: ይህ የያሲን ስጦታ ነው››

«አንቺ ራስሽም እንደ ያሲን ቅድስት ሳትሆኚ አትቀሪም›› አልኳት

አፈረች:: ፊቷ ቀላ ‹‹Don't talk rot›› አለችኝና ሲጋራውን አጠፋችው:: ምላሷ እንደገና ብቅ ብሎ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ለመሳተፍ ስላልቻልኩ መብራቱን አጠፋሁላቸውና የእብድ ሳቄን ቀጠልኩ

አሁን ሳስበው ምንም የሚያስቅ ነገር አልነበረም



# አምስት

ኤክስ ሰልችቶኝ ነበር፡፡ በፋሲካ በዓል ምክንያት የአንድ አስር ቀን እረፍት ስለነበረን፣ እና ይልቁን ሚረይ የምትባል ፈረንሳዊት እንሂድ ስላለችኝ፣ ወደ ኒስ ሄድኩና ሁለት ሳምንት አብሬአት አሳለፍኩ

ኤክስ ስመለስ (ማታ ነበር) ውሃ ጠምቶኝ ስለነበረ አንድ ካፌ ገብቼ ቢራ አዘዝኩ፡፡ አስታጥቂ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ፡፡ ወፍራም ቀይ ፊቱ ላይ እንደ ማሽላ ቆሎ ከፈለሱበት ብጉሮች አንዷን እየቆነጠጠና በህመም ፊቱን እያጨማደደ ‹‹ከመጣህ እየሰን አግኝተሽዋል?›› አለኝ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሁላችንም መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ሰበሰበን፡፡ ያሲንም እዚያ ነበር››

‹‹እሺ››

‹‹እና ዲስኩር አደረገልን››

‹‹ማን? አየለ?››

‹‹አዎን››

‹‹ምን አይነት ዲስኩር?››

‹‹ይሄ ያሲን እየዞረ ሆሞ ነው /ወንድ የሚወድ ወንድ/ ጆርናሊስት ነው/ ጋዜጠኛ/ እያለ ስሜን ያጠፋልና እባካችሁ አስታግሱልኝ›› አለን

‹‹ያሲን ስሜን ያጠፋል አለ?››

‹‹አዎን››

‹‹ከዚያስ?››

‹‹ያሲን ይሄን ካደ››

‹‹ከዚያስ?››

‹‹ከዚያ አየለ መጣና ያሲንን ‹‹አላደረግኩትም ካልክ እምንሃለሁ፣ ደስ እያለኝ እምንሃለሁ›› አለና ሳመው፡፡ ከዚያ ስብሰባው ተበተነ፡፡ ያበደ አይመስልህም?››

‹‹አይመስለኝም›› አልኩትና ተነስቼ ሂሳቤን ከፍዬ ከካፌው ልወጣ ስል፣ እሱም ሂሳቡን እየከፈለ



‹‹ወዴት ነው የምትሄደው?›› አለኝ

‹‹እኔ ሳላይህ ቀስ ብለህ በጥንቃቄ የተከተልከኝ እንደሆነ ወዴት እንደምሄድ ለማወቅ ትችላለህ›› አልኩት

በኩርፊያ ድምጽ ‹‹ለምንድን ነው የምከተልህ?›› አለኝ

‹‹ለጥያቄህ መልስ ለማግኘት›› አልኩትና ልሄድ ስል

‹‹ትላንትና ካዲሳባ ደብዳቤ ደረሰኝ›› አለኝ፡፡ በጣም ሊነግረኝ የፈለገው ነገር በሃሳቡ እንዳለ ያስታውቃል፡፡ መጥፎ ነገር መሆን አለበት

‹‹ጥሩ›› አልኩት

‹‹የሻረግ ታጨች›› አለ፡፡ ሆዴ ተንቦራጨቀ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ልቤ በሃይል መምታት ጀመረ፡፡ ጉልበቴ ውሃ ሆነ፡፡ የሻረግ ታጨች? ረሳችኝ በቃ? አስታጥቂና ጓደኞቹ ጉድ አደረጉኝ? አጣሉን በቃ? ውሸት መተማመንን እንቃንቆ አፈረሰው? ማን ይሆን ያጨት?

‹‹ገና ዛሬ መስማትህ ነው?›› አልኩት

‹‹ቀድመህ ሰምተህ ኖሯል?›› አለኝ አንጿን ብጉሩን እያሻሸ

‹‹አዎን›› አልኩት



http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ታዲያ ምነው አልነገርከኝ?›› አለኝ

‹‹ደግሞ ውሸት ፈጥረህ እንዳታፋርሳት ብዬ ነው››

‹‹ለምን አፋርሳታለሁ?››

‹‹ከዚህ በፊት ለምን አፋረስካት? ለራስህ ፈልገሀት እምቢ ስላለችህ ነዋ! ግን አንተን እምቢ በማለቷ አትፍረድባት፡፡ አስበው እስቲ፡፡ ቅርጽህ የተቀለበች ሴት ይመስላል፡፡ ንግግርህ ሁል ጊዜ የሴቶች የቡና ወሬ ነው፡፡ ምንህ ወንድ ሆኖ ሴቶች ሊወዱህ ይችላሉ? ኧረ ሰመሆኑ ቱላ አለህ? ወይስ ሀጢአትህን በብጉሮችህ አፍ ነው የምትተፋው?››

ሲቆነጥጣት የነበረውን ብጉር ቶሎ ለቀቃት፡፡ እዚያው ትቸው ሄድኩ ‹‹ነጃሳ! ቂጥ ፊት›› እያልኩ እየተናደድኩ ወደ አየለ ቤት አመራሁ፡፡ አራት ሰዓት ተኩል ነበር፡፡ ማታ፡፡



# ስድስት

በሩን ሳንኳኳ በአማርኛ ‹‹ማነህ?›› አለኝ ድምፁ የደነገጠ ይመስላል፡፡ ‹‹እኔ ነኝ ክፈት›› አልኩት

በሩን ሲከፍት የክፍሉ ሽታ መታኝ፡፡ እጁ ቀዘቀዘኝ፣ ደም ሙትቻ አጨባበጥ ሆነብኝ

‹‹በጣም ስፈልግህ ነበር፣ ግባ›› አለኝ፡፡ መልከ መልካም ፊቱ ላይ ይንቀባረር የነበረው ኩራት አሁን የለም፡፡ በሱ ቦታ የተዘረዘረ ከርዳዳ ጢም ይታያል፡፡



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰበሰብኩና እንዳይደበድቡኝ፣ እንዲተውኝ አስታግሱልኝ አልኳቸው››

‹‹ማንን ነው የሚያስታግሱልህ?››

‹‹የሚሰድቡኝን ሰዎች››

‹‹ማናቸው የሚሰድቡህ?››

‹‹ሁሉም በሄድኩበት ይሰድቡኛል››

‹‹አይተሃቸዋል?››

‹‹አላየኋቸውም። ሁል ጊዜ እየተደበቁ ነው የሚሰድቡኝ››

‹‹እሺ። አስታግሱልኝ ካልካቸው በኋላስ?››

‹‹እነዚያ ስድባቸውን ቀጠሉ። ይህን ስምንት ቀን ከክፍሌ አልወጣሁም። ለእራት እንኳን አልሄድም። ብስኩት፣ ሻይ ቡና ነው የምበላው። ሃያ ፓኮ ሲጋራና ሶስት ፓኮ ብስኩት ገዝቼ እዚችው ተዘግቼ ነው የምውለው የማድረው››

‹‹ምን ትሰራለህ?››

‹‹አንድ ጥናት ይዣለሁ››

‹‹የምን ጥናት?››

‹‹ስለ ሃይማኖት›› አለኝና የሚያነባቸውን መፅሐፍት አሳየኝ



‹‹ይኼኛው የአይሁድ ሃይማኖትና የክርስቲያን ሃይማኖት እንዴት እንደሚገናኙ ይናገራል፣ ይሄ የታወቁትን ሃይማኖቶች በሙሉ ያነጻጽራል። ይሄኛው. . . ››

ሰባት መፅሐፎች፣ ሰባቱም ስለ ሃይማኖት። ከአርእስታቸውና ከማውጫቸው እንዳየሁት፣ አንዱም ስለኮሙኒዝም አይናገርም፣ አንዱም ስለሬቮሉሽን አይጠቅስም። ሬቮሉሽን! ክፍሉ ለምን እንደተለወጠብኝ አሁን ገና ገባኝ። ውስጡ ተዝረክርከው በቀይ ቀለማት ‹‹REVOLUTION›› የሚል ነበልባል ሰው አይን ላይ ይወረውሩ የነበሩት መጽሄቶች አሁን የሉም። አንዷም የለችም። ሰባቱንም መፅሐፎች ካሳየኝና ስለነሱ ከነገረኝ በኋላ

‹‹አሁን አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው ያጣሁት›› አለኝ

‹‹ምን መፅሐፍ?››

‹‹መፅሀፍ ቅዱስ››

‹‹እኔ አለኝ። ላምጣልህ?››

‹‹አምጣልኝ››

‹‹እሺ ነገ ጥዋት ይዤልህ እመጣለሁ። እስከ አሁን ከጥናትህ ምን አገኘህ?›› አልኩት



http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ይሄኛው እንደሚለው፣ ማምለክ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ባህሪይ ነው፡፡ እንደ መብላት፣ እንደ ማሰብ፣ እንደ ግብረ ስጋ ነው፡፡ ታዲያ ምንም ሳልበድላቸው ሆሞ ጆርናሊስት ይሉኛል፡፡ ምኔ ነው ሆሞ? ምኔ ነው ጆርናሊስት? አንተና ያሲን ታውቁኛላችሁ፡፡ ከናንተ ጋር ነው የምውለው፡፡ እራቴንም የምበላው ከናንተ ጋር ነው፡፡ ታዲያ ምኔ ነው ሆሞ? ለምን እንዲህ ይሉኛል?››

‹‹ማናቸው እንዲህ የሚሉህ?››

‹‹እነሱ፡፡ ኮሪደር ሆነው፣ ከበሩ ኋላ ተሰብስበው ‹‹ሆሞ፣ ጆርናሊስት፣ እያሉ ያወራሉ፣ ይንሾካሾካሉ፣ ይጮሃሉ፡፡ ተኝቼ ሳለሁ ‹‹ራሲስት›› ይሉኛል፡፡ እስቲ እኔ መቼ ዘር አለያለሁ? ሰዎች ሁሉም ወንድሞቼ ናቸው፡፡ እነሱ ግን ሆሞ፣ ጆርናሊስት፣ ራሲስት ይሉኛል››

የሚናገረውን ብከደው ምናልባት ይሻል ይሆናል በማለት ‹‹አይሉህም›› አልኩት

‹‹ይሉኛል፡፡ እኔ ብቻየን፣ የሚያግዘልኝ የለ፡፡ ከእናቴ ተለይቼ ሰው ሀገር መጥቼ፣ ብቻየን አግኝተው ያጠቁኛል፡፡››



‹‹አይዞህ! ከእንግዲህ እኔ አለሁ፡፡ ልክ ልካቸውን እነግራቸዋለሁ፡፡ ከዚያ ዝም ይላሉ››

‹‹እምቢ ቢሉህስ?››

‹‹አይሉኝም››

‹‹ቢሉህስ?››

‹‹ኢምባሲያችን ስልክ እንደውልና ልክ እናስገባቸዋለን አይዞህ››

‹‹ምን አደረጓቸው? ጢሜን ስላሳደኩ ተቀይመውኝ ይሆን? ልላጨው?››

‹‹ካሰኘህ ተላጨው››

‹‹ደስ ይላቸው ይሆን?››

‹‹እነሱ ግድ የላቸውም፡፡ ላንተ እንደተመቸህ አድርግ››

‹‹ልላጨው?››

‹‹ተላጨው››

‹‹በቃ ልላጨው?››

‹‹በቃ ተላጨው››

‹‹በምላጭ ልላጨው?››

‹‹ተላጨው››

‹‹ከዚያ በኋላ ይተውኛል?››

‹‹ይተውሃል››



http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹አንተ ታግዝልኛለህ?››

‹‹ጓደኛህ አይደለሁም?››

‹‹እንግዲህ ካንተ ጋር ሲያዩኝ አይደፍሩኝም?››

‹‹አይደፍሩህም››

‹‹ኧረ እንኳን መጣህልኝ! እንኳን ደረስክልኝ! እምላክ ነው የታረቀኝ፡፡››

ወደ ላይ እያየና እጆቹን ወደ ላይ እያርገበገበ ‹‹እምላክ ነው የታረቀኝ! እንኳን ደረስክልኝ! እምላክ ነው የታረቀኝ!›› እያለ ተነስቶ፣ ለቤተክርስቲያን የሚሰግድ ይመስል ጎንበስ ብሎ ተንበርክኮ እግሬ አጠገብ ያለውን ቆሻሻ ወለል በአፉና በግንባሩ ይሳለም ጀመር

‹‹ተነስ፣ ተነስ›› እያልኩ ትከሻውን ይዤ አስነሳሁት፡፡ እንባው ይወርዳል፡፡ እንባው የእፎይታ ተንፈስ ማለት ነው፡፡ እንባው እየወረደ ፈገግ ተሳጨ፡፡ አልጋው ግርጌ በነበረው ቆሻሻ ፎጣ ፊቱን አደረቀ

‹‹አሁን ላጨሁት፡፡ በምላጭ ላጨሁት፡፡ እንግዲህ ምንም አይሉኝም››

‹‹ቢሉህም እኔ አለሁልህ፡፡ አይዞህ! በል ደህና እደር፡፡››



‹‹በሩን ልቆልፈው?››

‹‹ቆልፈው››

‹‹ልቆልፈው? ከውስጥ?››

‹‹እዎን ቆልፈው?››

‹‹መስኮቱንም ልዝጋው?››

‹‹ዝጋው››

‹‹መስኮቱን ዘግቼ በሩን ልቆልፈው በቃ፡፡ ከውስጥ በቁልፍ እቆልፈዋለሁ፡፡››

‹‹ደህና እደር››

‹‹ደህና እደር፡፡ አንተ ትሄዳለህ፣ እኔ በሩን እቆልፈዋለሁ››

‹‹ጥሩ››

‹‹ከውስጥ እቆልፈዋለሁ››

‹‹ቆልፈው፡፡ ደህና እደር››

‹‹እንኳን አንተ መጣህልኝ፡፡ እንግዲህ በሩን ቆልፌው እተኛለሁ››

‹‹ጥሩ››

‹‹መስኮቱን እዘጋዋለሁ››

‹‹ዝጋው››

‹‹ጎሽ! እንኳን አንተ መጣህ እንጂ ከእንግዲህ መስኮቱን ዘግቼ፣ በሩን ቆልፌ፣ አልጋ ውስጥ ገብቼ፣ ትራስ ተንተርሼ፣ ለጥ ማለት ነው››



http://ethioliberty.wordpress.com/

ያሲን ስለ አየለ ነብር ያለኝን አስታወስኩ:: ያፈቅርሃል ነበር ያለኝ:: አየለ በግጥም የተናገረ መሰለኝ:: አጋጣሚ ይሆን?

‹‹ጥሩ:: በል ደህና አደር›› አልኩትና ወጥቼ በሩን ዘጋሁ:: በሩን ሲቆልፍ ሰማሁት:: ሰፊ ጥልቅ ሀዘን ተሰማኝ:: በጣም ፈራሁ:: የሰው አዕምሮ ሲናወጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነበር



# ሰባት

በነጋታው ረፋድ ሲል ወደ ቤቱ ሄድኩ:: ሻይ አፈላሁለት:: የሻይ ጀበናው ቆሽሿል፣ ስኒዎቹ እንኳን ሊታጠቡ ተለቅልቀው የሚያውቁ አይመስሉም፣ ነጭ ሸክላቸው በቆሻሻ ብዛት ግራጫ ሆኗል፤ የፊት መታጠቢያውም እንደዚሁ ንጣቱን ረስቷል

የምሳ ሰዓት ሲደርስ ወደ ምግብ ቤት አልሄድም አለ:: አይዞህ እኔ አለሁ ብዬ ወሰድኩት:: ስንበላ ማንንም አልገላመጠ፣ ማንንም አላየ፣ ራሱን



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሼክስፒርን እንደ ሎራንስ ኦሊቪዬ አድርጎ የሚጫወተው የለም››

‹‹ሆም! ራሲስት! ጆርናሊስት! ኢምፔሪያሊስት! እያሉኝ'ኮ ነው። ምናለ ከኔ ጋር ብታመሽ?››

‹‹አይሉህም። በል ደህና እደር››

‹‹ካንተ ጋር ልምጣ?››

‹‹እሺ ምን ቸገረኝ››

‹‹ካንተ ጋር ልምጣ በቃ። ሰር ሎራንስ ኦሊቭዬን አብረን እናየዋለን። ጥሩ! ‹‹To be or not to be, that is the question›› ሲል አብረን እንሰማዋለን፣ አይደለም?››

‹‹አዎን››

ሲኒማው ውስጥ በጨለማ ሀምሌትና የአባቱ ጣዕረ መስኮት ሲገናኙ፣ አየለ ከጎኔ ‹‹ምንድነው?›› አለኝ

‹‹ምኑ?›› አልኩት

‹‹ይሄ ነገር አስደነገጠኝ። ልቤ ፈራ›› አለኝ። እኔ ሰራሴ ከፊልሙ አንዲት ቃል እንዳታመልጠኝ ጆሮየን አሹዬ አዳምጣለሁ፣ እሱ እዚህ ይለፈልፍብኛል። ዝም አልኩት። ሀምሌትና ያባቱ



ጣዕረ መስኮት ንግግራቸውን ቀጠሉ። አየለ ‹‹እኔ ፈራሁ›› አለኝ

‹‹ታዲያ ውጣ!›› አልኩት በሽቴ

‹‹አብረኸኝ ውጣ›› አይለኝም?!

‹‹ፊልሙስ?›› አልኩት። ከጎናችን አንዱ ኢሽ! አለን። እውነቱን ነው።

አየለ ‹‹ትመለሳለህ›› አለኝ ‹‹ውጭ አድርሰኸኝ ትመለሳለህ››

ዝም አልኩትና ፊልሙን ሳይ

‹‹እባክህ አስወጣኝ! ፈራሁ፣ ክፉኛ ፈራሁ!›› አለኝ

‹‹ኢድያ! ና እንውጣ›› አልኩት

ከጨለማው የፊልም አዳራሽ ወጣን። በትኬት ቆራጯ አጠገብ ስናልፍ አየለ ለጥ ብሎ እጅ ነሳትና በሚለማመጥ ድምጽ

‹‹Bon soir, madame›› አላት። ሌላ ጊዜ ቢሆን አፍንጫውን ነፍቶባት ባለፈ ነበር። ውጪ እንደደረስን ‹‹በል ልመለስ›› አልኩት

‹‹እዚህ ትተኸኝ?›› አለ ዙሪያውን በፍርሃት እየተመለከተ። የከተማው መብራት ወለል ብሎ በርቷል



http://ethioliberty.wordpress.com/

‹‹ምን ላውራልህ?››

‹የሆነ ነገር አውራልኝ:: ብቻ ዝም አትብለኝ::›› ብቻውን፣ የእብደት ምድረ በዳ ውስጥ ብቻውን፣ ሆሞ ራሲስት ጆርናሊስት እያሉ የድምጽ አውሬዎች እያሳደዱት ብቻውን፣ ከሰላ ፍሰጋ ይንከራተታል፣ ለመሸሸግ ይሞክራል፣ ወደ ጤነኛው አለም የሚወስደውን መንገድ ፍለጋ ይደናበራል:: መንገዱ ይኖር ይሆን? የኛ ድምጽ ትንሽ ተስፋ ይሰጠዋል:: የሚሽከረከረው የእብደት ምድረ በዳ ከጤነኛው አለም ጋር በክር ተንጠልጥሏል:: ክሩ ቢበጠስ' ምድረበዳው እንደ እንዝርት ሽክርክር እያለ ይፈናጠራል፣ በጣም ያስፈራዋል:: የኛ ድምጽ ነው ክሩ:: ዝም ያልን እንደሆነ በደነገጠ ድምጽ ‹‹አውሩ እንጂ›› ይለናል

ከነፌ ወጥተን ወደ ምኝታ ቤቱ ሄድን:: እንደገባን

‹‹ሻይ ላፍላልህ?›› አለኝ

‹‹አሁን ጠጣሁ'ኮ›› አልኩት

‹‹ምናለ ላፍላልህ››

‹‹የለም አልፈልግም››



‹‹ተው ላፍላልህ›› (አሁንም የትንሽ ልጅ ብልሃት)

‹‹የለም መሄድ አለብኝ››

‹‹ብቻዬን እዚህ ትተኸኝ?››

‹‹አድርሰኸኝ ትመለሳለህ አላልከኝም ነበር እንዴ?›› አልኩት

‹‹ምናለ አብረኸኝ ብትቆይ ልጄ? ሆሞ፣ ጆርናሊስት ራሲስት ኢምፔሪያሊስት! እያሉኝ እኮ ነው››

እኔው ሻይ አፍልቼ አጠጥቼው ሳጫውተው ከቆየሁ በኋላ

‹‹በል ተኛ›› አልኩት

‹‹ትተኸኝ ልትሄድ?››

‹‹እዚህ ላድር አልችልም መቼም››

‹‹ባይሆን እንቅልፍ እስኪመጣልኝ አጫውተኝ››

እምቢ ልለው አልቻልኩም:: እንቅልፉ ሲመጣ እንደ ትንሽ ልጅ አልጋ ውስጥ አስገብቼው፣ መብራቱን አጥፍቼለት፣ በሩን ከውጭ ቆልፌ ቁልፉን በበሩ ስር ወደ ውስጥ አሾልኬለት ሄድኩ:: ትንሽ ልጅ ሆኖ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ነበር። በፍርሃት ታስሮ የቅዠት ጨለማ ውስጥ የሚፍጨረጨር ትንሽ ልጅ



# ስምንት

እኔና ያሲን ሀኪም ቤት እንውሰድህ ብንለው እየለ በጭራሽ እምቢ አለ። ደጋግመን ለመንነው፤ ደጋግሞ እምቢ አለን። ምክንያቱን ሊነግረን አልፈለገም።

እንግዲህ አልፎ አልፎ ሻል ይለዋል። አንዳንዴማ ኩራትና ንዴቱ አይመለስም እንጂ ያው የድሮው እየለ ይሆናል። ያን ጊዜ ፊቱ ላይ ከባድ ድካም፤ አይኖቹ ውስጥ ሰፊ ሀዘን ይታያል። ብዙ አይናገርም። መስኮቱ ፊትለፊት ወምበር ላይ ቁጭ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ጫል፡፡ ከመታጠቢያው በላይ ያለው መስታወት ሳይቀር ተወልውሏል፡፡ ይህን ሁሉ ማነው የሰራው?

እስታጥቂ ነው፡፡ በጣም ገረመኝ፡፡



# ዘጠኝ

አንድ ቀን ለጊዜው ተሽሎት ሁለታችን ቁጭ ብለን ስናወራ ‹‹ሕባክህ ሀኪም ጋ እንውሰድህ›› አልኩት

አይኖቹ በፍርሃት እየፈጠጡ ‹‹እምቢዮ! ሀኪም አልፈልግም እምቢዮ!›› በጣም ጮኸና እየተርበተበተ ፊቴ ተንበርክኮ ጣቶቼን በፀሎት እያጣመረ ‹‹አደራህን!›› አለኝ

ሲያሳዝን! ኩሩ ሰው ተንበርክኮ እስከመለመን ሲደርስ ማሳዘኑ! ‹‹እሺ ተነስ፡፡ አንተ ካልፈቀድክ ማንም ቢሆን አይወስድህም፡፡ አይዞህ ተነስ›› እያልኩ አስነስቼ ወምበር ላይ አስቀመጥኩት፡፡ ሻይ አፍልቼ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ብዚህች ምሳጭ እዚህ መዳፌ ስር ያስቻውን የደም ስር እበጥሳታለሁ። ከዚያ ቀስ ብሎ እንቅልፍ ይወስደኛል። ብል ጀህና ሁን ልተኛ ነው። እሰና እጄን ዘረጋልኝ ... ተምበርክኬ እጁን ሳምኩት። በዝግታ ሰተምበረከኩበት አስነሳኝ። በሩን ከፈተልኝ። በቁልፉ ሲዘጋው ተሰማኝ።

አ.አ. የካቲት ፲፱፻፶፱ ዓ.ም



http://ethioliberty.wordpress.com/



ተምበርክኬ እጁን ሳምኩት፡፡
በዝግታ ከተምበረከኩበት አስነሳኝ፡፡
በሩን ከፈተልኝ፡፡ በቁልፍ ሲዘጋው
ተሰማኝ፡፡

DFB
AMH Igz
Igziabher, Sibhat Gebre
Sebatejaw Melak 2008
hutl 1
03010928532001

ፋር - ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅ. ዋጋው ብር:- 15.00

http://ethioliberty.wordpress.com/